## በረጂና የሚገኙ የኪድስፈርስት አጋሮች እነማን ናቸው?

- አግል ኸርት ማዕከል
- ረጂና የቅድመ ትምህርት ማዕከል
- ረጂና ኦፕን ዶር ሶሳይቲ
- ሬይንቦው የወጣቶች ማዕከል
- የመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ

## በኪድስፈርስት ፕሮግራም መሳተፍ የሚችሉት እንዴት ነው?

- ለበለጠ መረጃ ይደውሉልን ወይም ድረ ገፃችንን ይጎብኙ
- ሁኔታውን ለመገምገም ቀጠሮ ለማስያዝ— በ 306-766-6340 ይደውሉ
- ሪፈር ለማድረግ ድጋፍ የሚያደርግልንን አንድ ኤጀንሲ መጠየቅ ይችላሉ


**KidsFirst**

**1550 14th Avenue**
**Regina, Saskatchewan  S4P 0W6**
**306-766-6340**
**KidsFirstRegina.com**


Saskatchewan
**Health Authority**

*ኪድስፈርስት ረጂና ከሳስካቺዋን የጤና ባለስልጣን ጋር አጋር ሆኗል*

# KidsFirst
# Regina

**እርጉዝ ከሆኑ ወይም ዕድሜው 2 ዓመት ወይም ከዚያ የሚያንስ ህፃን ልጅ ያለዎት ከሆነ፣**
**ኪድስፈርስት ለእርስዎ የሚሆን ፕሮግራም ነው!**



## የቤት ለቤት ጉብኝት ፕሮግራም

• ጥንካሬ ላይ የተመሠረተ • ነፃ • በአማራጭነት የቀረበ

## ኪድስፈርስት ምንድን ነው?

ኪድስፈርስት ነፃ፣ በበጎ ፈቃደኝነት የሚሰራ ጤናማ የልጅ እድገት እና ከሰው ጋር ሊኖራቸው የሚችለውን ትስስር እና ፍቅር ለመደገፍ የተዘጋጀ የቤት ለቤት ጉብኝት ፕሮግራም ነው፡፡

## ኪድስፈርስት ለእርስዎና ለቤተሰብዎ ማድረግ የሚችለው ምንድን ነው?

መጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ወሳኝ ናቸው፡፡ የኪድስፈርስት ዓላማ ወደ ሕይወትዎ አዲስ ህፃን በሚያመጡበት ጊዜ ቤተሰብዎን መደገፍ ነው፡፡
ህፃኑ ከመወለዱ አስቀድሞም ሆነ ከተወለደ በኋላ ቤተሰቦች የኪድስፈርስት ድጋፍ እና አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፡፡



## ኪድስፈርስት የሚሰራው እንዴት ነው?

*“የእኔ የቤት ለቤት ጎብኚ እጅግ በጣም ጥሩ አድማጭ ስትሆን ውስጣዊ ጥንካሬና በራስ መተማመን እንዲኖረኝ አድርጋኛለች፡፡”*

ግምገማ ፕሮግራሙ ለእርስዎ ተስማሚ መሆኑን ለመወሰን እገዛ ያደርጋል፡፡ ተስማሚ ከሆነ፣ የቤት ለቤት ጎብኚ በሳምንት አንድ ጊዜ ይጎበኝዎትና በጣም ጥሩ ልጆች የማሳደግ ተግባራትን ለእርስዎ በማጋራት ቤተሰብዎ እየጨመረ በሚመጣበት ጊዜ ድጋፍ ያደርግልዎታል፡፡

*“የተሻለ ወላጅ እንድሆን፣ ልጄን እንዳዳምጥና ከልጄ ጋር ባለኝ ግንኙነት ትዕግስተኛ እንድሆን አነሳስተሸኛል፡፡”*

## የቤት ለቤት ጎብኚው የሚከተሉትን በማድረግ ግቦችዎን እንዲያሳኩ ያግዝዎታል:-

- ማዳመጥ
- በቤተሰብዎ ጥንካሬ ላይ መገንባት
- ወላጅነት እና የልጅ እድገትን በሚመለከት መረጃ መጋራት
- ለእርስዎ እና ለልጅዎ የአዕምሮ እድገትን የሚያበረታቱ የመዝናኛ ተግባራትን ያቀርባል
- እርስዎን ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት

## የኪድስፈርስት ቡድን አባላት የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ድጋፍ ያደርጉልዎታል፡--

- አስቸጋሪ ጉዳዮችን እንዲቋቋሙ
- ልማዳዊ የሆኑ ባህላዊ ትምህርቶችን መርምሮ በማወቅ በሥነ-ስርዓቶች ላይ እንዲሳተፉ

*“የተሻለ ወላጅ እንድሆን፣ ልጄን እንዳዳምጥና ከልጄ ጋር ባለኝ ግንኙነት ትዕግስተኛ እንድሆን አነሳስተሸኛል፡፡”*

